**የፍትሐብሔር ጉዳዮች በተመለከተ ለጠቅላላ ትእዛዙ የተሰጠ ተጨማሪ መግለጫ (አደንደም)**
**በኦገስት 27፣ 2020 የሻሻለ**

በተከታታይ በተላለፉ ትእዛዞች፣ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤት ዋና (ቺፍ) ዳኛ፣ የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ የተወሰኑ ቀነ-ገደቦች ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ በማለት አዟል። ዋና (ቺፍ) ዳኛው በቅርቡ ያስተላለፈው ትእዛዝ በኦገስት 13፣ 2020 ያወጣው ነው። በ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/matters-docs/General%20Order%20pdf/Amended-Order-8-13-20-FINAL.pdf *ይመልከቱ*፡ የኦገስት 13ቱ ትእዛዝ የፍትሐብሔር ክፍል በተመለከተ እንደሚከተለው አቅርቧል፡

> በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ እንዲፈጸሙ በህጎች (ክስ የሚቀርብባቸው ቀነ-ገደቦችም (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽን) ጭምር)፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ ቀነ-ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ፣ ነገር ግን እንዲህ የማይሆንባቸው የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች አሉ፡ (1) የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ገደብ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) በስተቀር፣ በሂደት ባሉ ጉዳዮች በጠበቃ የተወከሉ አካላት የሚመለከቱ ቀነ-ገደቦች፣ (2) በጠበቃ ላልተወከሉ አካላት ጭምር የሚመለከት ለሁሉም አካላት የሚመለከቱ ከግኝት (ዲስካቨሪ) ጋር የተያያዙ ቀነ-ገደቦች፣ እና (3) ከማርች 18፣ 2020 በኋላ በተላለፉ ቀነ ሰሌዳ ትእዛዞች ያሉ ቀነ-ገደቦች።

**የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ (ጁዲሽያል ኢመርጀንሲ)።** ኦገስት 13 በወጣው ትእዛዝ የተጠቀሰው ትእዛዝ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አስቸኳይ ጊዜ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤቶች ጆይንት ኮሚቴ ኦን ጁዲሽያል አድሚኒስትሬሽን (የፍትህ አስተዳደር የጋራ ኮሚቴ) በማርች 18፣ 2020 ያወጀው የአስቸኳይ ጊዜ ትእዛዝ ነው። https://www.dccourts.gov/sites/default/files/divisionspdfs/committee%20on%20admissions%20pdf/Joint-Committee-on-Judicial-Administration-for-the-District-of-Columbia-Courts-March-18-2020-Order.pdf *ይመልከቱ*፡ በጆይንት ኮሚቲ (የጋራ ኮሚቴ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ዋና (ቺፍ) ዳኛው የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜው ቢያንስ እስከ ኖቨምበር 9፣ 2020 ድረስ አራዝሞታል። ስለዚህ፣ ኦገስት 13 በተላለፈው ትእዛዝ ከተጠቀሱት ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፕሽንስ) በስተቀር፣ ቀነ-ገደቦቹ በአሁኑ ጊዜ እስከ ኖቨምበር 9 ድረስ ታግደዋል፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ቆመዋል (ቶል ተደርገዋል)፣ ተራዝመዋልም።

**ወሰን (ስኮፕ)**። ኦገስት 13 በተላለፈው ትእዛዝ ከተጠቀሱት ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፕሽንስ) በስተቀር፣ በኦገስት 13 ትእዛዝ መሰረት የታገዱት፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት የቆዩት (ቶል የተደረጉት)፣ እና የተራዘሙት የሚከተሉትና ሌሎችም ናቸው፡ (1) ክስ የሚቀርብባቸው ቀነ-ገደቦች የያዙ ህጎች (ስታቹስ ኦፍ ሊሚቴሽንስ)፣ (2) ደንብ-ተኮር ቀነ-ገደቦች፣ ለምሳሌ የሰነዶች ማድረሻ ሂደት (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) ቀነ-ገደቦች፣ ለግኝት ጥያቄዎች ምላሽ መስጫ፣ እና ወደ ቅድመ-ክርክር (ፕሪትራያል) ኮንፈረንስ የሚመሩ ክስተቶች፣ እና (3) እንደነ የመርሐግብር ትእዛዞችና መከራከርያ ጽሁፍ ማቅረቢያ ትእዛዞች የመሳሰሉ ከማርች 18፣ 2020 በፊት የተሰጡ ጉዳይ-ተኮር ትእዛዞች።

አዲሱ ቀነ-ገደብ የሚወሰነው፣ ጊዝያዊው ከተፈጻሚነት ማቆሚያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ በሚያበቃበት ቀን ነው። በኦገስት 13 በወጣው ትእዛዝ፣ ወይም ዋና (ቺፍ) ዳኛው አስቀድሞ ባወጣቸው ትእዛዞች፣ ያሉ ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፕሽንስ) ለጉዳይዎ የሚመለከቱ ካልሆነ፣ ጊዝያዊው ከተፈጻሚነት ማቆሚያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ፣ ኦገስት 13 በወጣው ትእዛዝ መሰረት፣ የሚያበቃበት ቀን ባሁኑ ጊዜ ኖቨምበር 9 ይሆናል፣ ከነዚህ ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፕሽንስ) መካከል አንዱ የሚመለከት ከሆነ ጊዜው ይቀድማል ማለት ነው። አዲሱ ቀነ-ገደብ በከፊል የሚወሰነው ቀነ-ገደቡ እንዲኖር ያደረገው ክስተት የተፈጸመው ከማርች 18 በፊት ነው ወይስ በኋላ በሚል ይሆናል፣ ይህ ቀን በዋና (ቺፍ) ዳኛው የመጀመሪያ ትእዛዝ መሰረት ጊዝያዊው ከተፈጻሚነት ማቆሚያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ የጀመረበት ነው። ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት የተፈጸመ ክስተት ቀነ-ገደቡ በጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ እንዲሆን ያደረገ ከሆነ፣ የመጀመሪያው ቀነ-ገደብ ከመጣሉ ከማርች 18 በፊት ቀርተው የነበሩ ቀናት፣ ጊዝያዊው ከተፈጻሚነት ማቆሚያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ መጨረሻ በሆነው፣ በኖቨምበር 9 ይጨመራሉ። ለምሳሌ፣ የሰነዶች ማድረሻ ሂደት (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ)፣ ለግኝት ጥያቄዎች ምላሽ መስጫ፣ ወይም አቤቱታን ለመቃወም የተሰጠ ቀነ-ገደብ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ ከተጀመረበት ማርች 18 አንድ ሳምንት ቀይቶ የነበረ ከሆነ፣ አዲሱ ቀነ-ገደብ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ ከተፈጸመ ከአንድ ሳምንት በኋላ ይሆናል። ቀነ-ገደቡን ያነሳሳው በጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ ክስተት ከሆነ የሰአቱ ቆጠራ የሚጀምረው ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ በሚያበቃበት ቀን ይሆናል። ለምሳሌ፣ አንድ ከሳሽ ቅሬታው በማርች 18 እና ኖቨምበር 9 መሀከል ፋይል ያደረገ ከሆነ፣ እና በደንብ 4(m)(1)(A) መሰረት መጥሪያውና ቅሬታውን ለተከሳሹ በ60 ቀናት ውስጥ ማድረስ የሚቻል ከሆነ፣ ከሳሹ ለተከሳሹ ከኖቨምበር 9 በኋላ ባሉ 60

ቀናት ውስጥ ማድረስ ይችላል ማለት ነው። አካሉ በደንብ 33(b)(2) መሰረት ጥያቄዎችን (ኢንተሮጋቶሪስ) በ30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ካለበት ወይም በደንብ 12-1(e) መሰረት ለአቤቱታ ምላሽ በ14 ቀናት ውስጥ መስጠት ካለበት ተመሳሳዩ መርህ ተግባራዊ ይሆናል።

በጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) ክፍለ ጊዜ ምክኒያት፣ በኦገስት 13 ትእዛዝ መሰረት የሚተገበረው የተራዘመው ቀነ-ገደብ፣ የጉዳይዎ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለጉዳይዎ ተገቢ ከሆነ፣ ቀነ-ገደቡ መራዘምን የሚጠይቅ ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ሊያስፈልግዎ፡ ነገር ግን፣ አንድ አካል የሚፈልገው ቀነ-ገደብ የኦገስት 13 ትእዛዝ ከሚሰጠው ቀነ-ገደብ የተለየ ከሆነ፣ ቀነ-ገደቡን ለማሳጠር ወይም ለማራዘም ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ይኖርበታል።

ምንም እንኳን እርምጃው የሚወሰድበት ቀነ-ገደብ ባለው የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ ምክኒያት የታገደ፣ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶል ማድረጊያ) የተደረገበት ወይም የተራዘመ ቢሆንም፣ የኦገስት 13 ትእዛዝ ማንኛውም አካል እርምጃ እንዳይወስድ አያግድም።

**ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፐሽንስ)**። የኦገስት 13ቱ ትእዛዝ ቀነ-ገደቦች መታገድ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆም (ቶል መደረግ) እና ማራዘም በተመለከተ ለወጣው አጠቃላይ መርህ ሶስት ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፐሽንስ) ያስቀምጣል።

**የተወከሉ አካላት**። የመጀመሪያው ልዩ ሁኔታ (ኤክሰፐሽን) በህግ (ስታቹ)፣ ደንብ (ሩል)፣ ወይም ትእዛዝ መሰረት የተከሰቱ፣ የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) በስተቀር፣ በመጠባበቅ ላይ ባሉ ጉዳዮች በጠበቃ የተወከሉ አካላት የሚመለከቱ ቀነ-ገደቦች የሚመለከት ነው። ከወረርሽን ጋር በተያያዙ-ምክኒያቶች በጠበቃ የተወከለ አካል አንድን ስራ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ ቢፈልግ፣ አካሉ ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ይኖርበታል (ይህ የሚሆነው የሌላኛው አካል ስምምነት ለማግኘት ከሞከረ በኋላ ነው)።

ይህ በጠበቃ የተወከለ አካል የሚመለከት ልዩ ሁኔታ (ኤክስፐሽን)፣ ሌሎች በጉዳዩ ያሉ አካላት በጠበቃ ቢወከሉም ባይወከሉም ተግባራዊ የሚሆን ነው። አንድ በጠበቃ የተወከለ አካል በጠበቃ ያልተወከለን አካል፣ በሁለተኛው ልዩ ሀኔታ (ኤክሰፐሽን) ከታች በበለጠ በሙላት ከተገለጸው ከግኙት-ጋር ተያያዥነት ያለው ቀነ-ገደብ ያልሆነ ቀነ-ገደብ እንዲያከብር የፈለገ ከሆነ፣ ጠበቃ የሌለው አካል በፈቃደኝነት የተጠየቀውን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ አካሉ ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ይኖርበታል።

ይህ ልዩ ሁኔታ (ኤክሰፐሽን)፣ እና ከግኙት ተያይዥነት ያላቸው ቀነ-ገደቦች፣ በደንቦች 16(h)(1) እና 37(a)(1)(A) የሰፈሩ ማንኛውም ከግኙት ተያያዥነት ያለው ማመልከቻ ፋይል ከማድረግ በፊት አካላቱ ምክኒያታዊ ለሆነ ጊዜ ያህል ከግኙት የተያያዙ ነገሮች ለመፍታት መወያየት እንዳለባቸው የሚያትት መስፈርት፣ እንዲሁም ደግሞ በደንብ 16(c)(1) የሰፈረ ጠበቆች እና ጠበቃ የሌላቸው አካላት የቅድመ-ክርክር ኮንፈረንስ ከማድረጋቸው በፊት "በአካል" መገናኘት ይኖርባቸዋል የሚሉትን መስፈርቶች አይነካም። በማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ፣ ከአካላቱ መሀከል አንድ ወይም ሁሉም አካላት በአካል እንዳይገናኙ የሚያደርግ አጥጋቢ የሆኑ ምክኒያቶች ሊኖሯቸዋቸው ይችላል፣ እና በነዚህ ሁኔታዎች በቴሌፎን ወይም ቪድዮኮንፈረንስ መገናኘቱ ምክኒያታዊ አማራጭ ሊሆን ይችላል። በደንቦች 16(c)(1)፣ 37(a)(1)(A) እና 26(h)(1) የሰፈሩት "በአካል" የመገናኘት መስፈርቶች እንዲተዉ የማድረግና የማሻሻል ስልጣን ዳኞች አላቸው። የጉዳይ አካላት በአካል ሳይገናኙ አንድን ጉዳይ ለመፍታት ለመሞከር አስቀድመው ፈቃድ ሳይጠይቁ ቢሞክሩ፣ እና አካላቱ አስቀድሞ ፈቃድ በመጠየቅ ሳይሆን በማመልከቻ ወይም የጋራ ቅድመ-ክርክር መግለጫ በመጠቀም ለተወሰኑ ከወረርሽኙ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምክኒያቶች በአካል-ያልሆነ ስብሰባ አድርገው እንደነበረ ቢያሳውቁም ዳኛው ይህን ስልጣን መጠቀም ይችላል። አካላቱ ያልተገናኙ ከሆነና ከአካላቱ አንድ ወይም ሁለቱም አካላት በአካል መገናኘት ያልቻሉበት ከወረርሽኝ ጋር በተያያዘ አጥጋቢ የሆነ ምክኒያት ቢኖራቸውና አካላቱ ምክኒያታዊ በሆኑ አማራጭ ዘዴዎች ቢገናኙ፣ ወይም መገናኘት እንደሚችሉ ቢጠቁሙ፣ ዳኞች ከግኙት ተያያዥነት ባላቸው ማመልከቻዎች ሊወስኑ እንደሚችሉና የቅድመ-ክርክር ኮንፈረንሶች ሊያደርጉ እንደሚችሉ አካላት መጠበቅ ይችላሉ።

ይህ ልዩ ሁኔታ (ኤክሰፐሽን) በፍርድ ቤት እያንዳንዱን ጉዳይ ለይቶ በማየት ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ታግዶ ያለ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት የቆመ (ቶል የተደረገ) ወይም የተራዘመ የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) ቀነ-ገደቦች አይመለከትም። የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) ተያያዥነት ያላቸው ቀነ-ገደቦች ከዚህ አልተካተቱም፣ ምክኒያቱም የማህበረሰብ ጤና አሳሳቢ ነገሮች የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረስን ከባድ ያደርገዋል። ይህ አለመካተት፣ ከሳሽ በዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ (ጁዲሽያል ኢመርጀንሲ) የፍርድ ቤት መጥሪያ ለማድረስ ሙከራ ከማድረግ አይከለክልም።

ይህ ልዩ ሁኔታ የሚመለከተው በመጠባበቅ ላይ ላሉ ጉዳዮች ብቻ ነው። ስለዚህም፣ ምንም እንኳን ከሳሽ ሊሆን የሚችል አካል በጠበቃ የተወከለ ቢሆንም ክስ የሚቀርብባቸው ቀነ-ገደቦች (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽንን) ታግደው፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆመው (ቶል ተደርገው)፣ እና ተራዝመው ይቆያሉ።

**የግኝት ቀነ-ገደቦችን (ዲስካቨሪ ዴድላይንስ)።** ሁለተኛው ልዩ ሁኔታ (ኤክሰፕሽን)፣ በጠበቃ ላልተወከሉም አካላት ጭምር፣ ለሁሉም አካላት የሚመለከቱ ከግኝት የተያያዙ ጉዳዮች የሚመለከት ነው፣ እና እንደ ሶስተኛው ልዩ ሁኔታ ሳይሆን ከማርች 18 በፊት በተላለፉ ትእዛዞች ስላሉ ቀነ-ገደቦችም የሚመለከቱ ናቸው። በጠበቃ ለተወከሉ አካላት ይህ ሁለተኛው ልዩ ሁኔታ እንደ መጀመሪያው ልዩ ሁኔታ ነው እየሆነ ያለው፣ ምክኒያቱም ከግኝት ተያያዥነት ላላቸው ጉዳዮችም የሚመለከት ስለሆነ። ማንኛውም አካል ከግኝት ተያያዥነት ላለው ስራ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ ቢፈልግ የፈለገው አካል ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ይኖርበታል (ይህ የሚሆነው የሌላኛው አካል ስምምነት ለማግኘት ከሞከረ በኋላ ነው)።

የሚከተሉት ምሳሌዎች፣ ከማርች 18 በፊት የተላለፉት የመርሐግብር ትእዛዞች ታዛዥ መሆን የሚኖርባቸው ማናቸውንም ጉዳዮች በተመለከተ፣ ገላጭ ናቸው፣ በተጨማሪ በመጀመሪያው ልዩ ሁኔታ ስር በጠበቃ ላልተወከሉ አካላት የሚመለከቱ ናቸው። ማናቸውም አካል ከማርች 18 በፊት 14 ቀናት ቀድሞ ጥያቄዎች (ኢንተሮጋቶሪስ) የቀረበበት ከሆነ፣ በማርች 18 ትእዛዝ መሰረት የግኝት ቀነ-ገደብ የታገደበት፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት የቆየበት (ቶል የተደረገበት) እና የተራዘመበት ጊዜ በደንብ 33(b)(2) ከተደነገጉት 30 የጥያቄዎች (ኢንተሮጋቶሪስ) ምላሽ መስጫ ቀናት ውስጥ የሚቀሩት 16ቱ ቀናት በመሆናቸው፣ አካሉ ምላሽ ለማድረስ ከኦገስት 13 ጀምሮ 16 ቀናት ይኖሩታል ማለት ነው። አንድ አካል ከማርች 18 በኋላና ከኦገስት 13 በፊት ጥያቄዎች (ኢንተሮጋቶሪስ) የቀረቡበት ከሆነ አካሉ ከኦገስት 13 ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። አንድ አካል ከኦገስት 13 በኋላ ጥያቄዎች (ኢንተሮጋቶሪስ) የደረሱት ከሆነ አካሉ ጥያቄዎች (ኢንተሮጋቶሪስ) ከደረሱበት በኋላ ባሉ 30 ቀናት ውስጥ ምላች መስጠት ይኖርበታል።

በጠበቃ ያልተወከሉ ተሟጋቾች ከግኝት የተያያዙ ቀነ-ገደቦች ከኦገስት 13 በፊት መታገዳቸው ለጊዜው ተፈጻሚ የማይሆኑ (ቶል የሚደረጉ) መሆናቸው ወይም መራዘማቸው፣ወይም እግዶቹ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት መቆሞቹ (ቶል መደረግ) እና መራዘሞቹ በኦገስት 13 ማብቃታቸው ያላወቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በደንብ 37(a) መሰረት አንድ አካል ማመልከቻ ፋይል ከማድረጉ በፊት አካሉ፣ በጠበቃ የተወከለ ቢሆንም ባይሆንም፣ ሌላኛው አካል መቼ ግኝት ማቅረብ እንዳሚኖርበት በተመለከተ ያለውን ማንኛውም አለመስማማት ለመፍታት መሞከር ይኖርበታል ይላል፣ እና ግኝት እንዲሰጥ የተጠየቀ አካል ግኝቱን እንዲያቀርብ ፍርድ ቤት ማዘዝ እንደሚችል ደንብ 37(a) ያስቀምጣል። በጠበቃ ያልተወከለ አካል ግኝት ማቅረብ እንደሚኖርበትና እንደማይኖርበት እንዲሁም ደግሞ ግኝት ለማቅረብ ምክኒያታዊ የሆነ ቀነ-ገደብ ምን እንደሚሆን ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን ነገሮች ግምት ውስጥ ያስገባል።

**ከማርች 18 በኋላ የተላለፉ ትእዛዞች።** ሶስተኛው ልዩ ሁኔታ (ኤክሰፕሽን) ከማርች 18፣ 2020 በኋላ ለተላለፉ የመርሐግብር ትእዛዞች የሰፈሩ ቀነ-ገደቦች ማገድ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ማቆም (ቶል ማድረግ) እና ማራዘም እንደሌለ በግልጽ ያስቀምጣል። ይህ ልዩ ሁኔታ፣ ምንም እንኳን ከማርች 18 በኋላ የወጣው ትእዛዝ ዳኛው ስልጣኑ የወሰደው በዋና ዳኛ ከወጡ ለጠቅላላ መርህ የእግድ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ማቆያ (ቶል ማድረጊያ)፣ እና ማራዘሚያ ትእዛዞች በግልጽ የሰፈረ መሆኑ የማይገልጽ ቢሆንም፣ ይመለከታል። ይህ ልዩ ሁኔታ (ኤክሰፕሽን) ለማንኛውም መርሀግብር የያዘ ትእዛዝ፣ ምንም እንኳን ትእዛዙ "የመርሐግብር ትእዛዝ" ተብሎ ያልተመለከተ ቢሆንም፣ ይመለከታል። ማንኛውም አካል ከማርች 18 በኋላ በወጣውን ትእዛዝ ያለውን ማንኛውም ቀነ-ገደብ እንዲታገድ፣ ለጊዜው ተፈጻሚ እንዳይሆን (ቶል እንዲደረግ) ወይም እንዲራዘም ከፈለገ፣ ይህን ማድረግ የፈለገ አካል ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ይኖርበታል (ይህ የሚሆነው የሌላኛው አካል ስምምነት ለማግኘት ከሞከረ በኋላ ነው)።

ይህ የከማርች 18 በኋላ የተላለፉ ትእዛዞች የሚመለከት ልዩ ሁኔታ፣ እንደነ የግኝት መዝጊያ ቀነ-ገደብ የመሳሰሉ ማናቸውም ከግኝት ተያያዥነት ያላቸው ቀነ-ገደቦች ያካትታል። ምንም እንኳን ከማርች 18 በኋላ የተላለፈው ትእዛዝ በትእዛዙ በሰፈረ በተወሰነ ቀን አካላቱ ምላሽ እንዲሰጡ በግልጽ ባይጠይቅም፣ ማናቸውንም ከግኝት ታያያዥነት ያለው ቀነ-ገደብ አካላት ቀነ-ገደቡ በሚያስከብር ሁኔታ በቂ ጊዜ በመስጠት አካላት ምላሽ እንዲሰጡ ያስገድዳል። እንደዚህ ካልሆነ፣ እንደነ የግኝት ማጠናቀቂያ ቀነ-ገደብ የመሳሰሉ በትእዛዙ ያሉ ከግኝት የተያያዙ ቀነ-ገደቦች ትርጉም የሌላቸው ይሆናሉ።

አንድ አካል ከማርች 18 በኋላ በተሰጠው ትእዛዝ የሰፈረውን ቀነ-ገደብ ተግባራዊ ማድረግ የማይችል ከሆነ አካሉ ቀነ-ገደቡ እንዲራዘም ማመልከቻ ፋይል ማድረግ ይኖርበታል (ይህ የሚሆነው የሌላኛው አካል ስምምነት ለማግኘት ከሞከረ በኋላ ነው)።

በተቃራኒውም፣ ከላይ እንደ ተገለጸው፣ ከማርች 18 በፊት በተላለፉ ትእዛዞች ያሉ ማናቸውምን ቀነ-ገደቦች፣ በማርች 18 ወይም ከዛ በኋላ በወጣ ትእዛዝ፣ ፍርድ ቤቱ በተቃራኒው ካላዘዘ በስተቀር ወይም በኦገስት 13 በወጣው ትእዛዝ የሰፈረ ልዩ ሁኔታ የሚመለከት ከሆነ በስተቀር፣ ታግዷል፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆሟል (ቶል ተደርጓል)፣ ተራዝመዋልም።

**የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) ጉዳዮች።** በመይ 7፣ 2020 የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) ጉዳዮች በተመለከተ የተላለፈው አጠቃላይ ትእዛዝ፣ በከንቲባዋ በታወጀው የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ እና ከመጠናቀቁ በፊት ባሉ 60 ቀናት ውስጥ ፋይል የተደረጉ ወይም በመጠባበቅ የነበሩ በአስተዳደር-የተመደቡ (አድሚኒስትሬቲቭሊ-ደዚግኔትድ) የእዳ ስብሰባ ጉዳዮች ቀነ-ገደቦች በተመለከተ በተለየ ይናገራል። https://www.dccourts.gov/sites/default/files/matters-docs/General%20Order%20pdf/Collection-Case-General-Order.pdf *ይመልከቱ።* ይህ ትእዛዝ፣ በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ ሁሉም ክስ የሚቀርብባቸው ቀነ-ገደቦች (ስታቹስ ኦፍ ሊሚቴሽን) እና የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) ቀነ-ገደቦች ጨምሮ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና በቆሙና በሌሎች ትእዛዞች ያሉ ቀነ-ገደቦችና የጊዜ-ገደቦች፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማለቅ ይገባቸው የነበረ በዚህ ክፍለ ጊዜ ለጊዜው ከተፈጻሚነት እንደሚቆሙ (ቶል እንደሚደረጉ) ያቀርባል።

**የመኖሪያ ቤት ሀራጅ (ሞርጌጅ ፎርክሎዠር) ጉዳዮች።** በጁላይ 2፣ 2020 የወጣው የመኖሪያ ቤት ብድር ሀራጅ (ረዚደንሻል ሞርጌጅ ፎርክሎዠር) ጉዳዮች በተመለከተ አጠቃላይ ትእዛዝ፣ በከንቲባዋ በታወጀው የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ እና ከመጠናቀቁ በፊት ባሉ 60 ቀናት ስለሚነሱ የመኖሪያ ቤት ሀራጅ (ሞርጌጅ ፎርክሎዠር) ጉዳዮች አስተዳደር ጉዳይ በተመለከተ ምላሽ ይሰጣል። https://www.dccourts.gov/sites/default/files/matters-docs/General%20Order%20pdf/General-Order-for-Foreclosure-Cases-7-2-20.pdf *ይመልከቱ።*

**ቀነ ቆይታ (ጁሬሽን)።** ይህ ለጠቅላላ ትእዛዙ የተሰጠ ተጨማሪ መግለጫ (አደንደም) ሁኔታዎች በመቀየራቸው ምክኒያት እስኪሻሻል ወይም እስኪሰረዝ ድረስ በስራ ላይ ይቆያል።

የፍትሐብሔር ክፍል ዋና ዳኛ (ፕሪሳይዲንግ ጃጅ) በሰጡት ትእዛዝ በኦገስት 27፣ 2020 ተሰጠ።

**[ተፈርሞበታል]**
**ላውራ ኤ. ኮርዴሮ**
**ዋና ዳኛ (ፕሪሳይዲንግ ጃጅ)፣ የፍትሐብሔር ክፍል**